የመድኃኒዓለም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን - የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
MARCH 20220

***መግቢያ***

*ያለንበት ወቅት ዓለማችን በብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች እያለፈች መሆኑ ሁላችን የምንመሰክረው ሐቅ ነው። በቅርቡ ከተከሰተው የቫይረስ ስርጭት የተነሳ የዓለም ሕዝቦች በአስቸጋሪ ኤኮኖሚያዊ፡ ፖለቲካዊና ማህበረሰባዊ ቀውስ ወስጥ ናቸው። ኃያላን ናቸው የሚባሉ አገሮች እንኳን ሳይቀሩ ለችግሩ መፍትሔ ለማግኘት አልቻሉም። ከዚህም የተነሳ በጣም ብዙ ሕዝቦች- አማኞችም ሳይቀሩ - ብፍርሃትና በጭንቀት ውስጥ ናቸው።*

*እንደዚህም ሆኖ ግን እግዚአብሔር ዛሬም በዙፋኑ ላይ ነው: ሁሉንም ደግሞ ይገዛል (መዝሙር* 103: 19)። *በተጨማሪም "እግዚአብሔር ግን በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤ ምድርም ሁሉ በፊቱ ዝም ትበል"* (*ዕንባቆም* 2:20) *ተብሎ የተፃፈለት አምላክ ከተደመጠ በዚሁ በአስቸጋሪ ወቅትም የሚናገረው ይኖረዋል። መ/ቅዱስ እንደሚያስተምረን የእግዚአብሔር ቃል* 1) *ትክክለኛ ነው፡* 2) *የሚያጸና ነው፡* 3) *ለተቀበለው መልካም ነው። በዚህም ምክንያት ቤ/ክርስቲያናችን ወቅታዊና አስፈላጊ በሆኑ መጽሓፍ ቅዱሳዊ ሓሳቦች ዙርያ ጥናትና ጸሎት እንዲደረግ በመወሰን ሁሉም አባሎች እንዲካፈሉና በእ/ር ቃል እንዲጽናኑ በትህትና ትጠይቃለች።*

ጥናት 01 **- ወደ እግዚአብሔር መመለስ**

የንባብ ክፍል: **ትንቢተ ኢዮኤል 1:1 – 2:17**

*1:1 ወደ ባቱኤል ልጅ ወደ ኢዩኤል የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው። 2 እናንተ
ሽማግሌዎች፥ ይህን ስሙ፤ በምድርም የምትኖሩ ሁሉ፥ አድምጡ። ይህ በዘመናችሁ ወይስ በአባቶቻችሁ
ዘመን ሆኖ ነበርን? 3 ይህን ለልጆቻችሁ ንገሩ፤ ልጆቻችሁም ለልጆቻቸው፥ ልጆቻቸውም ለኋለኛው
ትውልድ ይንገሩ። 4 ከተምች የቀረውን አንበጣ በላው፤ ከአንበጣም የቀረውን ደጎብያ በላው፤ ከደጎብያም
የቀረውን ኩብኩባ በላው። 5 በተሃ ወይን ጠጃችሁ ከአፋችሁ ተወግዶአልና እናንተ ሰካራሞች፥ ነቅታችሁ
አልቅሱ፤ እናንተም የወይን ጠጅ የምትጠጡ ሁሉ፥ ዋይ በሉ። 6 ቍጥርም የሌለው ብርቱ ሕዝብ በምድሬ
ላይ ወጥቶአልና፤ ጥርሳቸው እንደ አንበሳ ጥርስ፥ መንጋጋቸውም እንደ እንስቲቱ አንበሳ መንጋጋ ነው። 7
ወይኔን ባዶ ምድር አደረገው፥ በለሴንም ሰበረው፤ ባዶም አደረገው፥ ጣለውም፤ ቅርንጫፎቹም ነጡ። 8*

ለቍንጅናዋ ባል ማቅ ለብሳ እንደምታለቅስ ድንግል አልቅሺ። 9 የእህሉ ቍርባንና የመጠጡ ቍርባን
ከእግዚአብሔር ቤት ተወግዶአል፤ የእግዚአብሔርም አገልጋዮች ካህናቱ አለቀሱ። 10 እህሉ ጠፍቶአልና፥
ወይኑም ደርቆአልና፥ ዘይቱም ጐድሎአልና እርሻው ምድረ በዳ ሆኖአል፥ ምድሪቱም አልቅሳለች። 11
መከሩ ከእርሻቸው ጠፍቶአልና ገበሬዎች ስለ ስንዴውና ስለ ገብሱ አፈሩ፤ የወይን አትክልተኞችም
አለቀሱ። 12 ወይኑ ደርቆአል፥ በለሱም ጠውልጎአል፤ ሮማኑና ተምሩ እንኰዩም የምድርም ዛፎች ሁሉ
ደርቀዋል፤ ደስታም ከሰው ልጆች ዘንድ ርቆአል። 13 የእህሉ ቍርባንና የመጠጡ ቍርባን ከአምላካችሁ
ቤት ቀርቶአልና እናንተ ካህናት፥ ማቅ ታጥቃችሁ አልቅሱ፤ እናንተም የመሠዊያ አገልጋዮች፥ ዋይ በሉ፤
እናንተ የአምላኬ አገልጋዮች፥ ኑ፥ ሌሊቱን ሁሉ በማቅ ላይ ተኙ። 14 ጾምን ቀድሱ፥ ጉባኤውንም አውጁ፤
ሽምግሌዎችንና በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ቤት ሰብስቡ፥ ወደ
እግዚአብሔርም ጩኹ። 15 የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአልና ለቀኑ ወዮ! እርሱም ሁሉን ከሚችል ከአምላክ
ዘንድ እንደ ጥፋት ይመጣል። 16 ከዓይናችን ፊት ምግብ፥ ከአምላካችንም ቤት ደስታና እልልታ የጠፉ
አይደለምን? 17 ዘሩ በምድር ውስጥ በሰበሰ፤ እህሉ ደርቆአልና ጎተራዎቹ ባዶ ናቸው፥ ጎታዎቹም
ፈርሰዋል። 18 እንስሶች እጅግ ጮኹ፤ የላምም መንጎች ማሰማርያ የላቸውምና ተጠራጠሩ፤ የበግም
መንጎች ጠፍተዋል። 19 አቤቱ፥ እሳት የምድረ በዳውን ማሰማርያ በልቶአልና፥ ነበልባሉም የዱሩን ዛፍ
ሁሉ አቃጥሎአልና ወደ አንተ እጮኻለሁ። 20 ፈሳሹ ውኃ ደርቆአልና፥ እሳቱም የምድረ በዳውን
ማሰማርያ በልቶአልና የምድር አራዊት ወደ አንተ አለኸለኹ።

2:1 የእግዚአብሔር ቀን መጥቶአልና፥ እርሱም ቀርቦአልና በጽዮን መለከትን ንፉ፥ በቅዱሱም
ተራራዬ ላይ እሪ በሉ፤ በምድርም የሚኖሩ ሁሉ ይንቀጥቀጡ፤ የእግዚአብሔር ቀን መጥቶአልና፤ 2
የጨለማና የጭጋግ ቀን፥ የደመናና የድቅድቅ ጨለማ ቀን ነው፤ ታላቅና ብርቱ ሕዝብ በተራሮች ላይ እንደ
ወገግታ ተዘርግቶአል፤ ከዘላለምም ጀምሮ እንደ እነርሱ ያለ አልነበረም፥ ከእነርሱም በኋላ እስከ ብዙ
ትውልድ ድረስ እንደ እነርሱ ያለ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም። 3 እሳት በፊታቸው ትባላለች፥
በኋላቸውም ነበልባል ታቃጥላለች፤ ምድሪቱ በፊታቸው እንደ ዔድን ገነት፥ በኋላቸውም የምድረ በዳ በረሃ
ናት፤ ከእነርሱም የሚያመልጥ የለም። 4 መልካቸው እንደ ፈረስ መልክ ነው፥ እንደ ፈረሶችም ይሮጣሉ። 5
በተራራ ላይ እንዳሉ ሰረገሎች ድምፅ፥ ገለባውንም እንደሚበላ እንደ እሳት ነበልባል ድምፅ፥ ለሰልፍም
እንደ ተዘጋጀ እንደ ብርቱ ሕዝብ ያኰበኵባሉ። 6 ከፊታቸው አሕዛብ ይንቀጠቀጣሉ፤ የሰውም ፊት ሁሉ
ይጠቍራል። 7 እንደ ኃያላን ይሮጣሉ፥ እንደ ሰልፈኞችም በቅጥሩ ላይ ይወጣሉ፤ እያንዳንዱም በመንገዱ
ላይ ይራመዳል፥ ከእርምጃቸውም አያፈገፍጉም። 8 አንዱ ካንዱ ጋር አይጋፋም፥ እያንዳንዱም መንገዱን

ይጠበጥባል፤ በሰልፍ መካከል ያልፋሉ፥ እነርሱም አይቈስሉም። 9 በከተማም ያኰበኵባሉ፥ በቅጥሩም ላይ
ይሮጣሉ፤ ወደ ቤቶችም ይወጣሉ፥ እንደ ሌባም በመስኮቶች ይገባሉ። 10 ምድሪቱም ከፊታቸው
ትናወጣለች፥ ሰማያትም ይንቀጠቀጣሉ፤ ፀሐይና ጨረቃም ይጨልማሉ፥ ከዋክብትም ብርሃናቸውን
ይሰውራሉ። 11 እግዚአብሔርም በሠራዊቱ ፊት ድምፁን ይሰጣል፤ ሰፈሩ እጅግ ብዙ ነውና፥ ቃሉንም
የሚያደርግ እርሱ ኃያል ነውና፤ የእግዚአብሔርም ቀን ታላቅና እጅግ የሚያስፈራ ነውና ማንስ ይችለዋል?
12 አሁንስ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ በፍጹም ልባችሁ፥ በጾምም፥ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ። 13
ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ፤ አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ፥ ቍጣው የዘገየ፥
ምሕረቱም የበዛ፥ ለክፋትም የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ። 14 የሚመለስና የሚጸጸት እንደ ሆነ፥
ለአምላካችሁም ለእግዚአብሔር የእህልና የመጠጥ ቍርባን የሚሆነውን በረከት የሚያተርፍ እንደ ሆነ ማን
ያውቃል? 15 በጽዮን መለከትን ንፉ፥ ጾምንም ቀድሱ፥ ጉባኤውንም አውጁ፥ 16 ሕዝቡንም አከማቹ፥
ማኅበሩንም ቀድሱ፥ ሽማግሌዎቹንም ሰብስቡ፥ ሕፃናቱንና ጡት የሚጠቡትን አከማቹ ሙሽራው
ከእልፍኙ፥ ሙሽራይቱም ከጫጉላዋ ይውጡ። 17 የእግዚአብሔርም አገልጋዮች ካህናት ከወለሉና
ከመሠዊያው መካከል እያለቀሱ፦ አቤቱ፥ ለሕዝብህ ራራ፥ አሕዛብም እንዳይነቅፉአቸው ርስትህን
ለማላገጫ አሳልፈህ አትስጥ፤ ከአሕዛብ መካከል፦ አምላካቸው ወዴት ነው? ስለ ምን ይላሉ? ይበሉ።

1. የንባብ ክፍሉ በኅብረት ይነበብ።

2. ያለንበት ወቅት በኢዮኤል ዘመን ከነበረው ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር እንዴት ይመስላል? (በኢዮኤል ዘመን የምድሪቱ ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ: የሕዝቡ ስጋዊና መንፈሳዊ ሁኔታና የ እ/ር ምላሽ እንዴት እንደነበር ይነጋገሩ)
   ……………………………………………………………………………
   ……………………………………………………………………………
   ……………………………………………………………………………
   ……………………………………………………………………………
   ……………………………………………………………………………
   ……………………………………………………………………………

3. በዛሬው የንባብ ክፍል መሰረት ዓለም ስትናወጥ፡ ፈተናዎችና ችግሮች ሲበዙ፡ የ እ/ር ሰዎች ምላሽ ምን መሆን አለበት ይላሉ? (መልሱ በኢዮኤል 1፡13;19 እና 2፡12- 13 ማግኘት ይችላሉ።)

   ……………………………………………………………………………
   ……………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………

…………………………………………………

I. እ/ር ሕዝቡ በፈተና እንዲያልፍ የሚፈልገው ለምንድን ነው ይላሉ? በሌላ አነጋገር አሁን የምናየው የቫይረስ ወረርሽኝ ለምን መጣ ብለው ያስባሉ?.................................................................................

.................................................................................

.................................................................................

............................. (በተጨማሪ ያዕቆብ 1፡1-4 ያንብቡ።)

II. የዘመኑን የቫይረስ ችግር ለመወጣት አንዳንዱ ሰው መጸለይ ብቻ ነው ያለብን ብሎ ሲያስብ: ሌላው ግን ጸሎትም ያስፈልጋል፡ ሳይንስ የሚለውም መስማት ጠቃሚ ነው ይላል:: እርስዎ ከየትኛው ወገን ነዎት? ለምን?

.................................................................................

.................................................................................

.................................................................................

.................................

4. በምዕራፍ 1:13 “የእህሉ ቍርባንና የመጠጡ ቍርባን ከአምላካችሁ ቤት ቀርቶአልና እናንተ ካህናት፥ ማቅ ታጥቃችሁ አልቅሱ፤ እናንተም የመሠዊያ አገልጋዮች፥ ዋይ በሉ፤ እናንተ የአምላኬ አገልጋዮች፥ ኑ፥ ሌሊቱን ሁሉ በማቅ ላይ ተኙ።” የሚል ቃል እናነባለን።

I. እ/ር ሕዝቡ እንዲያለቅስ የጠየቀው ለምንድን ነው?

………………………………………………………………………

………………………………………………………………………

………………………………………………………………………

…………………………

II. በዚህ ዘመን አማኞች ብዙ በእ/ር ፊት ሲያለቅሱ አይታዩም፡ ቤ/ክርስቲያንም ይህንን ስታስተምር አትታይም፡ ይህ ለምን ሆነ ብለው ያስባሉ?

.................................................................................

.................................................................................

.................................................................................

.................................................................................

...........................................

III. በዮሐንስ 11፡35 "ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ" የሚል ሲያነቡ፡ እንደ እየሱስ ተከታይና እርሱን ለመምሰል እንደሚተጋ ሰው ራስዎን እንዴት ይገመግማሉ?

..........................................................................................
..........................................................................................
..........................................................................................
..........................................................................................
..........................................

5. በምዕራፍ 1:13-14 መሰረት ማልቀስ ያለበት ማን ነው?

..........................................................................................
..........................................................................................
..........................................................................................
................................................................................

I. የተጻፉት ሰዎች ተርታ ሲያነቡ ምን ያስተውላሉ?

..........................................................................................
..........................................................................................
..........................................................................................
................................................................................

6. በምዕራፍ 2፡12 "አሁንስ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ በፍጹም ልባችሁ፥ በጾምም፥ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ።" የሚል እናነባለን። ወደ እ/ር መመለስ ማለት ምን ማለት ነው?

..........................................................................................
..........................................................................................
..........................................................................................
................................................................................

I. አማኞች ወደ እ/ር መመለስ ያለባቸው ምክኒያቶች ምንድን ናቸው ይላሉ? (በተጨማሪ ሉቃስ 13:1-5 ያንብቡ።)

..........................................................................................
..........................................................................................
..........................................................................................
..........................................................................................
..........................................

7. ኢዩኤል በምዕራፍ 2:1 "የእግዚአብሔር ቀን መጥቶአልና" ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህ የሚሆነው መቼ ነው?

..........................................................................................
..........................................................................................
..........................................................................................
......................................

8. አንድ ሰው ወደ እ/ር ለመመለስ ማድረግ ያለበት ምንድ ነው ይላሉ? (ምዕራፍ 2:13 እንደገና ያንብቡ)

.......................................................................................................

.......................................................................................................

.......................................................................................................

.....................................

9. በዛሬው የንባብ ክፍል መሰረት ወደ እ/ር መመለስ ያለበት መን ነው? (ምዕራፍ 2:15-16 ያንብቡ።)

.......................................................................................................

.......................................................................................................

.......................................................................................................

....................................... ("We will not see a repenting world until we see a repenting church" DL Moody)

10. አማኞች ወደ እ/ር መመለስ ያለባቸው መቼ ነው? (ምዕራፍ 2:12 ያንብቡ።)

.......................................................................................................

.......................................................................................................

.......................................................................................................

.......................................

ጥናት 02 **- የካሳ ዘመን**

የንባብ ክፍል: **ትንቢተ ኢዮኤል 2:18 – 2:27**

18 እግዚአብሔርም ስለ ምድሩ ቀና፥ ለሕዝቡም ራራለት። 19 እግዚአብሔርም መልሶ ሕዝቡን፦
እነሆ፥ እህልንና ወይንን ዘይትንም እሰድድላችኋለሁ፥ እናንተም በእርሱ ትጠግባላችሁ፤ ከእንግዲህም ወዲያ
በአሕዛብ መካከል መሰደቢያ አላደርጋችሁም። 20 የሰሜን ንም ሠራዊት ከእናንተ ዘንድ አርቃለሁ፥ ወደ
በረሃና ወደ ምድረበዳ፥ ፊቱን ወደ ምሥራቁ ባሕር ጀርባውንም ወደ ምዕራቡ ባሕር አድርጌ አሳድደዋለሁ፤
እርሱም ትዕቢትን አድርጎአልና ግማቱ ይወጣል፥ ክርፋቱም ይነሣል አለ። 21 ምድር ሆይ፥ እግዚአብሔር
ታላቅ ነገር አድርጎአልና አትፍሪ፥ ደስም ይበልሽ፥ እልልም በዪ። 22 እናንተ የምድር እንስሶች ሆይ፥
የምድር በዳው ማሰማርያ ለምልሞአልና፥ ዛፉም ፍሬውን አፍርቶአልና፥ በለሱና ወይኑም ኃይላቸውን
ሰጥተዋልና አትፍሩ። 23 እናንተ የጽዮን ልጆች፥ አምላካችሁ እግዚአብሔር የፊተኛውን ዝናብ በጽድቅ
ሰጥቶአችኋልና፥ እንደ ቀድሞውም የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ አዝንቦላችኋልና በእርሱ ደስ ይበላችሁ፥
ለእርሱም እልል በሉ። 24 አውድማዎችም እህልን ይሞላሉ፥ መጥመቂያዎችም የወይን ጠጅንና ዘይትን
አትረፍርፈው ያፈስሳሉ። 25 የሰደድሁባችሁ ታላቁ ሠራዊቴ አንበጣና ደጎብያ ኩብኩባና ተምች
የበላቸውን ዓመታት እመልስላችኋለሁ። 26 ብዙ መብል ትበላላችሁ፥ ትጠግቡማላችሁ፤ ከእናንተም ጋር
ተአምራትን የሠራውን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ስም ታመሰግናላችሁ፤ ሕዝቤም ለዘላለም
አያፍርም። 27 እኔም በእስራኤል መካከል እንዳለሁ፥ እኔም አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ፥
ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ታውቃላችሁ ሕዝቤም ለዘላለም አያፍርም።

1. በትንቢተ ኢዮኤል 2:18 – 2:27 የተጻፈው መልዕክት ዋና ሐሳብ ምንድ ነው?
   ………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………

2. የኢዮኤል ትንቢት የተተነበየው በእርሱ ዘመን ለነበሩ እስራኤላዊያን ቢሆንም መልዕክቱ ለኛም ጭምር ነው። በአሁኑ ዘመን ላለን አማኞች **"አንበጣና ደጎብያ ኩብኩባና ተምች የበላቸውን ዓመታት"** ምን ይመስላሉ?
   ………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………
   …

   i. ሕይወትዎን ሲመለከቱ: ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው/የትኞቹ እርስዎን ይመለከታሉ?

ከሌሉ ጥያቄውን ማለፍ ይችላሉ።

- ፍሬ-አልባ ዓመታት (ብዙ ለፍቶ በጣም ጥቂት ፍሬ ማግኘት)
- የሐዘን ዓመታት (በሕመም፡ ሞት፡ አለመሳካት ምክኒያት ወዘተ....)
- የራስ ወዳድነት ዓመታት
- ፍቅር-አልባ ዓመታት (ጥላቻ፡ ልዩነት፡ ጭቅጭቅ ወዘተ...የሞላባቸው ዓመታት)
- ያለመታዘዝ ዓመታት
- ትክክለኛ ያልሆነ ውሳኔ ወስነው የከሰሩበት ዓመታት
- ከክርስቶስ ውጭ የተኖረ ዓመታት (ከጌታ ጋር በወጣትነት ዘመን/ዕድሜ አለመገናኘት)

ii. ስለነዚህ "የተከሰሩ ዓመታት" ሲያስቡ ምን ይላሉ? (ከተቻለ በግልጽነት ተነጋገሩበት)

..............................................................................
..............................................................................
..............................................................................
..............................................................................
......

3. በዛሬው የንባብ ክፍል "18 እግዚአብሔርም ስለ ምድሩ ቀና፥ ለሕዝቡም ራራለት። 19 እግዚአብሔርም **መልሶ** ሕዝቡን......." የሚል ሓሳብ እናገኛለን? እ/ር የመለሰው የትኛውን ጸሎት ነው?

..............................................................................
..............................................................................
..............................................................................
..............................................................................
...

I. የጸሎቶቹ ትርጓሜ ምንድ ነው ይላሉ?

..............................................................................
..............................................................................
..............................................................................
........................

4. በትንቢተ ኢዮኤል 2:17 የተጻፈው ሐሳብ: በሮሜ 8፡32 ከተጻፈው ቃል ጋር ሲያነጻጽሩ እንደ አዲስ ኪዳን አማኝ ምን ይማራሉ?

..............................................................................
..............................................................................
..............................................................................
................................................

5. ያለፉትን ዓመታት መመለስ በሰው ችሎታ የሚሆን ነገር አይደለም። እግዚአብሔር ይህ ከሰው ችሎታ በላይ የሆነውን ነገር ማድረግ የሚችለው እንዴት ነው?
………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………
…

6. በቁጥር 27 "እኔም በእስራኤል መካከል እንዳለሁ፥……" የሚል እናነባለን። ይህንን ሐሳብ እንዴት ይረዱታል?
………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………
………………

   I. እንደ አዲስ ኪዳን አማኝ ይህ ለርስዎ ምን ማለት ይመስልዎታል? (ለበለጠ ማብራርያ ሉቃ. 7፡36-50 ያንብቡ።)
   ………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………
   ………………………

7. በቁጥር 26 "ብዙ መብል ትበላላችሁ፥ ትጠግቡማላችሁ፤……" የሚል እናነባለን። ይህንን ሐሳብ እንዴት ይረዱታል?
………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………
………………

   II. እንደ አዲስ ኪዳን አማኝ ይህ ለርስዎ ምን ማለት ይመስልዎታል? (ለበለጠ ማብራርያ ማቴ. 13፡8 ያንብቡ።)
   ………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………
   ………………………………………………

8. በ1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:7 "በዚህም እጅግ ደስ ይላችኋል፥ ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ፥

ለምስጋናና ለክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል……” የሚል ቃል አናነባለን። ይህ ቃል ዛሬ ካጠናነው ሐሳብ ጋር እንዴት ይያያዛል ይላሉ?

…………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………

ጥናት 03 - **እግዚአብሔር መንፈሱን ሲያፈስ…………**

የንባብ ክፍል: **ትንቢተ ኢዮኤል 2:28 – 2:32**

28 ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች
ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ ጐበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፤
29 ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ፤
30 በላይ በሰማይ ድንቆችን አሳያለሁ፥ በታች በምድርም ደምና እሳት የጢስም ጭጋግ።
31 ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ፥ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣል።
32 እንዲህም ይሆናል፤ የእግዚአብሔር ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል፤ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረ፥ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም መድኃኒት ይገኛል። ደግሞም እግዚአብሔር የጠራቸው፥ የምስራች የሚሰበክላቸው ይገኛሉ።

1. እግዚአብሔር በኢዩኤል በኩል መልዕክቱን ሲያመጣ ጊዜው (የሰዎቹ ሁኔታ) ምን ይመስል ነበር? ……………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………
2. በዛሬው የንባብ ክፍል መሠረት የእ/ር መንፈስ በፈሰሰ ጊዜ የሚሆኑ ነገሮች ምንና ምን ናቸው?

   ……………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………
   1. “ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ”፥ እና “ ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ፤ “የሚሉትን ሓሳቦች

እንዴት ይረዱዋቸዋል?

…………………………………………………………………………………

………..

3. ትንቢት ምንድን ነው? ጥቅሙስ? እውነተኛ ትንቢትስ እንዴት ይታወቃል? …………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………

4. በዘሁልቁ ምዕ. 11 ሙሴ የጸለየው ጸሎትና እና በሓዋ. ስራ ምዕ. 2:16-21 ጴጥሮስ የተናገረው ሲረዱ ስለ ትንቢት ምን ይላሉ?

…………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………

5. በነቢዩ ኢዩኤል የተነገረው እና በሓዋ. ስራ ምዕ. 2 የሆነውን ሲያነቡ፡ ዛሬ በዘመናችን እንደዚህ ዓይነቱ ነገር እየተፈጸመ ነው ይላሉ? ለምን?

…………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………

6. በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ፡ የእ/ርን ድምጽ የሚሰማ ሕይወት እንዲኖረን ማድረግ ያለብን ምንድ ነው ይላሉ? (ለማብራሪያ ሮሜ. 12፡1፤ የሐዋ. ስራ 5፡12 እና ኤፌ. 3፡19 ያንብቡ)። …………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………

ጥናት 04 **- የውሳኔ ቀን…………**

የንባብ ክፍል: **ትንቢተ ኢዮኤል 3:1 – 2:21**

1 እነሆም፥ በዚህ ወራትና በዚህ ዘመን፥ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ምርኮ በምመልስበት ጊዜ፥
2 አሕዛብን ሁሉ ሰብስቤ ወደ ኢዮሣፍጥ ሸለቆ አወርዳቸዋለሁ፤ በዚያም ስለ ሕዝቤና ስለ ርስቴ ስለ
እስራኤል በአሕዛብ መካከል የበተኑአቸውን ምድሬንም የተካፈሉአትን እፋረድባቸዋለሁ። 3 በሕዝቤም
ላይ ዕጣ ተጣጣሉ፤ ወንድ ልጅን ለጋለሞታ ዋጋ ሰጡ፥ ሴት ልጅን ለወይን ጠጅ ሸጡ፥ ጠጡም። 4
ጢሮስና ሲዶና የፍልስጥኤምም ግዛት ሁሉ ሆይ፥ ከእናንተ ጋር ለእኔ ምን አለኝ? በውኑ ብድራትን
ትመልሱልኛላችሁን? ብድራትን ብትመልሱልኝ ፈጥኜ በችኰላ ብድራታችሁን በራሳችሁ ላይ
እመልሳለሁ።
5 ብሬንና ወርቄን ወስዳችኋልና፥ የተወደደውንም መልካሙን ዕቃዬን ወደ መቅደሳችሁ አግብታችኋልና፥
6 ከዳርቻቸውም ታርቁአቸው ዘንድ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ልጆች ለግሪክ ሰዎች ሸጣችኋልና፥
7 እነሆ፥ እነርሱን ከሸጣችሁበት ስፍራ አስነሣቸዋለሁ፥ ብድራታችሁንም በራሳችሁ ላይ እመልሳለሁ።
8 እግዚአብሔር ተናግሮአልና ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁን በይሁዳ ልጆች እጅ እሸጣለሁ፥ እነርሱም
ለሩቆቹ ሕዝብ ለሳባ ሰዎች ይሸጡአችኋል። 9 ይህን በአሕዛብ መካከል አውጁ፤ ለሰልፍ ተዘጋጁ ኃያላንን
አስነሡ ሰልፈኞች ሁሉ ይቅረቡ ይውጡም። 10 ማረሻችሁን ሰይፍ፥ ማጭዳችሁንም ጦር ለማድረግ
ቀጥቅጡ፤ ደካማውም፡- እኔ ብርቱ ነኝ ይበል። 11 እናንተ በዙሪያ ያላችሁ አሕዛብ ሁሉ፥ ቸኵላችሁ ኑ፥
ተሰብሰቡ፤ አቤቱ፥ ኃያላኖችህን ወደዚያ አውርድ። 12 አሕዛብ ይነሡ፥ ወደ ኢዮሣፍጥ ሸለቆም ይውጡ፤
በዙሪያ ባሉ አሕዛብ ሁሉ ላይ እፈርድ ዘንድ በዚያ እቀመጣለሁና። 13 መከሩ ደርሶአልና ማጭድ ስደዱ፤
መጥመቂያውም ሞልቶአልና ኑ እርገጡ፤ ከፉታቸውም በዝቶአልና መጥመቂያ ሁሉ ፈርሶአል።
14 የእግዚአብሔር ቀን በፍርድ ሸለቆ ቀርቦአልና የብዙ ብዙ ሕዝብ ውካታ በፍርድ ሸለቆ አለ።
15 ፀሐይና ጨረቃ ጨልመዋል፥ ከዋክብትም ብርሃናቸውን ሰውረዋል። 16 እግዚአብሔርም በጽዮን ሆኖ
ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጮኻል፥ በኢየሩሳሌምም ሆኖ ቃሉን ይሰጣል፤ ሰማይና ምድርም ይናወጣሉ፤
እግዚአብሔር ግን ለሕዝቡ መሸሸጊያ፥ ለእስራኤልም ልጆች መጠጊያ ይሆናል። 17 እኔም በተቀደሰው
ተራራዬ በጽዮን የምቀመጥ አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ፤ የዚያን ጊዜም

ኢየሩሳሌም የተቀደሰች ትሆናለች፥ እንግዶችም ከእንግዲህ ወዲህ አያልፉባትም። 18 በዚያም ቀን እንዲህ
ይሆናል፤ ተራሮች በተሃ ጠጅ ያንጠባጥባሉ፥ ኮረብቶችም ወተትን ያፈስሳሉ፥ በይሁዳም ያሉት ፈፋዎች
ሁሉ ውኃን ያጐርፋሉ፤ ከእግዚአብሔርም ቤት ምንጭ ትፈልቃለች፥ የሰጢምንም ሸለቆ ታጠጣለች።
19 በአገራቸው ንጹሑን ደም አፍስሰዋልና በይሁዳ ልጆች ላይ ስላደረጉት ግፍ ግብጽ ምድረ በዳ፥
ኤዶምያስም በረሃ ይሆናል። 20 ነገር ግን ይሁዳ ለዘላለም፥ ኢየሩሳሌምም ለልጅ ልጅ መኖሪያ ይሆናል።
21 እኔም ንጹሕ ያላደረግሁትን ደማቸውን ንጹሕ አደርገዋለሁ፥ እግዚአብሔርም በጽዮን ያድራል።

1. የንባብ ክፍሉ በኅብረት ይነበብ::

2. በምዕራፍ 3:1 "እነሆም፥ በዚህ ወራትና በዚህ ዘመን፥ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ምርኮ በምመልስበት ጊዜ" የሚል ሐሳብ እናነባለን። ይህንን ሐሳብ እንዴት ይረዱታል? የሚሆንበት ጊዜስ መቼ ነው?

   ………………………………………………………………………………………
   …………
   ………………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………………
   ………………………………

   I. እ/ር ምርኮ በሚመልስበት ጊዜ የሚሆነው ምንድን ነው?
   ………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………
   ……………………………………………

3. በምዕራፍ 3:2-8 እ/ር የሚፈርድበትን ምክኒያቶች ይናገራል::  ከዚህ ስዕላዊ መግለጫ ምን የሚገነዘቡት ነገር አለ? በዚህ ዘመን ለምንኖር አማኞችስ ምን የሚያስተምረን ነገር አለ?………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………………
   ………………………………………………………………………………………
   ……………………………………………

I. እ/ር ምርኮ በሚመልስበት ጊዜ ፍርድ ያስፈለገው ለምን ይመስልዎታል?

........................................................................................................
........................................................................................................
........................................................................................................
..............................................................

4. በምዕራፍ 3:9-15 በእ/ር የፍርድ ጊዜ የሚሆነውን ኢዩኤል በስዕላዊ መግለጫ አቅርቦልናል። ከዚህ ክፍል ምን የሚያስተውሉት ነገር አለ?

..............................................................................................................
..............................................................................................................
..............................................................................................................
..............................................................................................................
.......................................................

   I. በዚህ ክፍል መሰረት አሕዛብ በፍርድ ሸለቆ ውጊያ የሚገጥሙት ከማን ጋር ነው? የእ/ር ቃል በ2ኛ ተ. 2፡8 ከሚናገረው ሃሳብ ጋር አያይዘው የመጨረሻው ውጤት ምን ይመስላል ይላሉ?

   ................................................................................................
   ................................................................................................
   ................................................................................................
   ................................................................................................
   ....................................................................

5. በምዕራፍ 3:16-21 እ/ር በፍርድ ጊዜ ለሕዝቡ የሚያደርገውን ያሳያል። ከዚህ ምን የሚያገኙት ትምህርት አለ?

........................................................................................................
........................................................................................................
........................................................................................................
........................................................................................................
...................................................................................

   II. በዚህ ክፍል "እግዚአብሔር ግን ለሕዝቡ መሸሸጊያ፥ ለእስራኤልም ልጆች መጠጊያ ይሆናል።" የሚል እናነባለን። የእ/ር ጠባቂነት ለእኛ ለአዲስ ኪዳን አማኞች የሚገለጸው እንዴት ነው?

   ................................................................................................
   ................................................................................................
   ................................................................................................
   ................................................................................................
   ....................................................................

III. የእ/ር ጠባቂነት በአማኞች ሕይወት: **automatic** (ጌታን ከተቀበልን ወዲያው የሚሆን ነገር) ነው ወይስ **conditional** (ጠባቂነቱ ሕይወታችን ከጌታ ጋር እስካስማማን ድረስ)?

.........................................................................................
.........................................................................................
.........................................................................................
.........................................................................................
................................................................